# የፍትሐ ነገሥት እውነተኛነት

ፍትሐ ነገሥት የሚባለው መጽሐፍ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ እንደሆነ በማመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ታላቅ ክብር ያለውና ቅዱስነትም የሚሰጠው ሕግ ነው። ከክብሩም ብዛት የተነሣ ማንም እየተነሣ አባላ እንዳይመታው፤ ለተለዩ ሰዎች በትምህርት መልክ ብቻ ሲሰጥ ቆይቷል፣ ጉባኤውም የሚኬደው በሰገነት ነበር፤ የሕግ ዐዋቂውም ሰው ይከበርና ሊቁ የመባልም ማዕረግ ይሰጠው ነበር። ብዙ የምርምር ሰዎች ግን ፍትሐ ነገሥቱ በሰገነት ይኬድ የነበረበት ምክንያት ከክብሩ ይልቅ ሁሉም የሕግ ሊቅ እንዳይሆን በምቀኝነት እንዲሠወር የተደረገ ዘዴ መሆኑን ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ ሁሉ ጥራዝ ነጠቅ እንዳይሆን ትምህርቱ ለሚከተትላቸው ደቀ መዛሙርት ብቻ ይሰጥ ስለነበር በሰገነት መኬድ ግድ ሆነበት ይላሉ። በዚያም ሆነ በዚህ ምክንያት በሰገነት መኬዱ ግልጥ መሆኑንና ሕግ ለሁሉም አለመዳረሱን ማመን ሲኖርብን ፍትሐ ነገሥቱ ግን ከፍ ያለ ክብርና ተፈላጊነትም እንደ ነበረው የታመነ ነው። መጽሐፉ በብዙ ሊቃውንት እጅ ባለመዋሉ ደግሞ ብዙ አቃቂር ሳይደረግበት ዕውነቱና ሐሰቱ ሳይገለጥበት ይኖራል፤ ማለት ሁሉም የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ ሳይሆን በየጊዜው የተደረጉ የዓለም ቤተ ክርስቲያንና የብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች ተገናኝተው የተቀመሩ መሆናቸውን የሚያውቁ በመጠኑ ናቸው። እንዲሁም ከጽርዕ የተተረጐመ እንደመሆኑ አብርሃም ቀሲስ ወደ ዓረብኛ ሲተረጉም ከራሱ ስሜት እያወጣ የጨመረበት ብዙ ይገኛል፤ በዚህ አንፃርም ከቀድሞው ውሳኔ ያስቀረው ሊኖር ይችል ይሆናል። ፍትሐ ነገሥት የሚል ስም የተሰጠውም ወደ ግዕዝ ሲተረጐም ሳይሆን አይቀርም፤ ውሳኔው ሥጋዊና መንፈሳዊ ሲሆን የነገሥት ፍትሕ መሆኑን ሲያመለክት የቤተ ክርስቲያን ድርሻ የሆነውን ፍትሕ የረሳ ይመስላል፤ ነገር ግን ነገሥታቱ የሃይማኖትም የአስተዳደርም ኃላፊነት እንደነበራቸው ለማስታውስ ያህል ነው በማለት ፍትሐ ነገሥት ብለውታል። እንዲያውም ሊቃውንቱ እንደሚያትቱት ፍትሐ ነገሥቱ ሊተረጐም የቻለው አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በተመኙት መሠረት መሆኑ እርግጥ ነው፤ ይኸውም አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በመጀመሪያ መናኝ የነበሩ ፍጹም መንፈሳዊ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ፤ ከርሳቸው በፊት ያልነበረ ለጊዜው ተመሳሳይ ከሕዝብ ጋር የሚያስተሣስር ሕግ ለሀገራቸው እንዲታወጅ ያስደረጉትም ከእውነተኛነታቸው የተነሣ መሆኑ ግልጥ ነው፤ እንዲያውም ዘርዓ ያዕቆብ ከሚለው ስያሜ ሌላ ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ የሚለው የማዕርግ ስያሜ የተሰጣቸው በዚሁ ሕግ ቀማሪነታቸው ነው፤ ምክንያቱም ቆስጠንጢኖስ ፫፻፲፰ቱን ሊቃውንት ሰብስቦ ለዘመኑ ተስማሚ የሆነ ሕግ እንዲሠሩለትና እንዲሰጡት እንደጠየቃቸው ሁሉ አጼ ዘርዓ ያዕቆብም ያገሩን ሊቃውንት ሰብስበው በዘመነ ወንጌል እየኖርኩ በሕገ ኦሪት እፈርዳለሁ፤ ስለዚህ ብሔራዊ ሕግ

ሊሆን የሚገባውን ሕግ ወስናችሁ ስጡኝ አሏቸው ፤ እነርሱም የንጉሡን ቀና አስተያየት የሃይማኖቱን ፍጹምነት የሐሳቡን ቅዱስነት ተመልክተው ወዲያውኑ ተሰብስበው አሁን ፊውስ መንፈሳዊ እየተባለ የሚጠራውን ሕግ ወስነው አቀረቡለት ይባላል ። ይኸም ሕግ ፍጹም መንፈሳዊ አመራርን ብቻ በተለይም ድርቅናን ያዘለ ሕግ እንጅ አህጉራዊ ፍትሕን የማይመለከት በመሆኑ ምኞቱ ያልተፈጸመለት መሆኑን በየጊዜው ይገልጥ እንደነበር ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለግብፃዊው ጴጥሮስ አብደል ሰይድ እንደገለጠለት እንረዳለን ። እርሱም ይህ ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ በዓረብኛ እንደሚገኝና ቢተረጐም ጠቃሚ መሆኑን ምኞቱም እንደሚፈጸምለት ገልጦ ነገረው ፤ እንግዲያውስ ከማንኛውም ሰው ይልቅ አንተው ፪ቱንም ዓይነት ቋንቋዎች ታውቃለህና ፈጽምልኝ ብሎ ስለጠየቀው ከዓረብ ወደ ግዕዝ ፍትሐ ነገሥትን ተርጒሞ እንደሰጠው በመቅድሙ ሊቃውንቶቻችን ያብራራሉ ። እንግዲህ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በመጀመሪያ ሊቃውንቱን እንደ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ብሔራዊ ሕግ እንዲሠሩለት ስለጠየቀ ፤ ቀጥሎም የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ በሀገሩ ቋንቋ ተተርጒሞ እንዲሠራበትና መንፈሳዊ አስተዳደር እንዲኖረው በመጣሩ የሕግ ሰው መሆኑን በግልጥ ለማስታወቅ ዘርዓ ያዕቆብን ቆስጠንጢኖስ ብለው ሰይመውታል ፤ ስለዚህም ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ ተብሏል ።

በፍትሐ ነገሥቱ ላይ ከአበው ውሳኔ ጋር ግብፃውያን በተለይ ያስቀመጡት ዕዝል ቅጥል « ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ መምህራኒሆሙ » የሚል ይገኛል ፤ ይኸም ከግል ፍላጐታቸው የተነሣ የደቀሉት ነው ። እርሱም ሥርዋጽ በሚለው ትእምርተ ጥቅስ እንጅ በተለመደው አጠቃቀስ በአንቀጽ ውስጥ የገባ አይደለም ። በዚህም መልክ ሥርዋፅ እያለ በየአንቀጹ መካከል የሚገባ ብዙ አለ ፤ እርሱንም በጥብቅ ሲመረምሩት አብርሃም ቀሲስ በራሱ ፈቃድ ያስገባው ይመስላል ፤ ትርጒሙም ሥርዋጽ ማለት « የጠመመ ማቅኛ የጐደለ መሙሊያ » ነው ይላሉ ፤ ስለዚህም ያልተቃና ሐሳብ ባለበት ሁሉ የራሱን ፍላጐት ለማሟላት ሲል በየቦታው አስገብቶበታል ለማለት ይቻላል ። ይኸም ዕንቅፋት የሆነ አንቀጽና ሌላም ይኸን የመሰለ አስቸጋሪ አንቀጽ እያለ በኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ቅዱስ ሕግ ፤ እየተባለ ሲከበር ይኖራል ። በቤተ ክርስቲያናችን አሁንም ቢሆን ሌላ ሕግ የለም ገናም አልወጣም ሆነም ቀረ የሚጠቀሰው ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ፤ ይኸም ማለት ክፋውንም ደጉንም እንዳዘለ ይዞ ይገኛል ማለት ነው ። በመንግሥት በኩል ግን ፍትሐ ነገሥቱ የምንጭነቱ ሥልጣን ሳይነፈገው በሕግ በኩል ራሱን የቻለ ሌላ ሕግ ሠርቶ እርሱን በመድበልነቱ ብቻ ይጠቀምበታል ። ፍትሐ ነገሥት በታሪክ በኩል ይኸን የመሰለ ዋጋ ሲኖረው ከላይ እንደገለጥኩት በቤተ ክርስቲያን አሁንም ገና የሕግነት ቦታውን እንደያዘ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በታሪክነቱም በሕግነቱም ቢሆን ብዙ ፈላጊ አለው ፤ ስለዚህም በአንድምታ ትርጓሜ ፤ በነጠላ ትርጓሜ በእንግሊዝኛ ታትሞ ይገኛል ። ወደፊት ግን ጊዜ ቢገኝ ግዕዙን አስተካክሎ

መተርጐም ሳያስፈልግ አይቀርም ። ፍትሐ ነገሥቱ በሕግነት መልክ ባይሠራበትም ቅሉ ሁሉም ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይላል የሚለውን ጥቅስ ለመስማት ይጓጓል ፤ ስለዚህ መጽሐፉን ለማንበብ ታሪኩን ለመስማት ምሥጢሩን ለመረዳት የሚፈልገው ብዙ ነው ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩/ በኢትዮጵያ የሕግ መጻሕፍት ብዙ መሆናቸውን ለመግለጥ ያህል ስማቸውን ሁኔታቸውን በመግለጥ ጻፍን እንጂ ።—

ሀ/ አደባባይ ወጥቶ የሚታወቀው ፤

ለ/ በጉባኤ የሚኬደው (የሚተረጐም) ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ።

፪/ ሌሎች የሕግ መጻሕፍት የሕግ መጻሕፍትነታቸው በፍትሐ ነገሥቱ ስለተገለጠ የኛ ቤተ ክርስቲያን ቀርታ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሕግ መጽሐፍ ሊስት ላይ ያስቀምጧቸዋል ፤ በኛ ግን የዓይን አንድም የንባብ መጽሐፍ ዋጋ የሚሰጣቸው ይመስላል ።

፫/ ሁሉም ታትመው አንድም ተባዝተው በየእጁ ለሁሉ ስላልተዳረሱ የብዙዎች መጻሕፍት ስማቸው እንጂ ዝርዝር ነገራቸው ሙሉ እንቀጻቸው አይደለም ።